# <u>ፓትሪስ ሉሙምባ-- በአፍሪካ ጠላቶች የተገደለ ጀግና</u>

ሀማ ቱማ




ፓትሪስ ሉሙምባ፣ ከነሞቡቱ ክህደት በሁዋላ በቤልጅም ወታደሮች ከመገደላቸው በፊት የተነሳ የመጨረሻው ፎቷቸው

He was put under house arrest, while a CIA officer was dispatched with a tube of poison toothpaste. Before his assassin arrived, Lumumba escaped from his house arrest, but rearrested from a plane in Elizabethville. He was beaten and humiliated in front of diplomats and journalists, and was on the truck that would inevitably carry him to his execution when the above picture was taken. It was Lumumba's last photo. A month later, he was executed — put up against a tree and shot by a firing squad directed, so it seems, by Belgian army officers. His body was buried on the spot, later dug up, and dissolved in acid. The bones were ground up and scattered to the winds to make sure there was nothing left of him. The colonel who deposed Lumumba, Joseph Mobutu (later Mobutu Sese Seko) would rule the country despotically until 1997 and proved to be an utter embarrassment for the West, with his Mao suits, cult of personality and nepotism. (http://iconicphotos.wordpress.com/2010/03/07/patrice-lumumba/)

ቅኝ ገዢዎች አፍሪካን ሲቀራመቱ ትንሺቷ ቤልጅም ኮንጎን ይዛ ለዓመታት በዝብዛለች። የንጉስ ሊዎፖልድ ወታደሮች ከ 15 ሚሊዮን ያላነሰ የኮንጎ ዜጎችንም መጨፍጨፋቸው ዛሬ በሰነድ የተረጋጋጠ ሀቅ ሆኗል። ኮንጎ የወርቅ፣ አልማዝና ልዩ ልዩ ማዕድናት ባለ ሀብት በመሆኑ ዘራፊዎቿ በጭካኔ መዝብረዋታል። በአሁኑ ወቅትም ቢሆን ወደ 6 ሚሊዮን የኮንጎተወላጆች በተለይም በምስራቅ ኮንጎ ምዕራባውያን በሚኒዷቸው የጦር አበጋዞችና ሚሊሺያዎች የተገደሉት የሀገሪቷን ምርጥማዕድን በተለይም ለኮምፒዩተርና ለእጅ ቴሌፎን በጣም አስፈላጊ የሆነውን ኮልታን የተባለውን ማዕድንና አያይዞም ወርቅና ሌሎችንም ማዕድኖች ለመቆጣጠር መሆኑ የታወቀ ነው።

ኮንጎ ከቤልጅም ነፃ ልትወጣ ስትነሳ የሕዝቡን ትግል መሪ ሆኖ ብቅ ያለው ፓትሪስ
ሉሙምባ የሚባል ሀገር ወዳድ ነበር። የነፃይቷ ኮንጎ የመጀመሪያው ጠቅላይ ሚኒስ
ቴር ሆኖ በዴሞክራሲያዊ መንገድ የተሰየመው ሉሙምባ በአሜሪካ ቤልጅም በተዘ
ጋጀ ሴራ በከሀዲዎቸ ተይዞ በጃንዋሪ 17/1961 (ጥር 9/1953 ዓ.ም.) በኤልሳቤትቪ
ል ከተማ በግፍ ተገደለ ። እጁ ወደ ኋላ ተጠፍሮ የፈረንጅ ቅጥረኞች ሲያንገላቱት
ፎቶው በዓለም አቀፍ ደረጃ የተሰራጨው ጀግናው ሉሙምባን ለመግደል የአሜሪካ
የስለላ ድርጅት (ሲ. አይ. ኤ) አውጥቷቸው የነበሩት ዕቅዶች ሁሉ ዛሬ ተጋልጠዋ
ል።

በመጨረሻ ይኸው የስለላ ድርጅትና ቤልጅም ተባብረውና እነ ኮለኔል ሞቡቱንም ተ
ጠቅመው ሉሙምባ ሊያስሩትና ሊገድሉት ችለዋል። ሞቡቱ፡ፀሐይ ስትወጣ ጀምሮ
በሲአይኤ የሚከፈለው ቅጥረኛ የነበረ በመሆኑ ሌሎች ተቀናቃኞቹን አስወግዶ (ቾ
ምቤን፣ ካዛቡቡን ወዘተ) የኮንጎ ፕሬዚዳንት ሆኖ ሀገሩን ሲበዘብዝና ሲያስበዘብዝ ቆይ
ቶ ቀኑ ሲደርስ ተገልብጦ (በሌላ የአሜሪካ ወዳጅ ካቢላ ትልቁ) በስደት ሞቷል።

ሉሙምባ ላይ ባዕዳኑ የሞት ፍርድ የፈረዱበት የኮንጎ ሀብት በቅድሚያ ለኮንጎ ሕዝ
ብ ጥቅምመዋል አለበት ብሎ በመናገሩና ክብሩን የጠበቀ፣ በአፍሪካ የሚኮራ ሀገር
ወዳድ በመሆኑና አፍቅሮ አፍሪካ አቅዋምን በማስተጋባቱ አለምንም መረጃ ኮሙኒስ
ት ተብሎ ተወግዞ መሆኑ በታሪክ ተመዝግቧል። ሉሙምባን የገደሉት ዘመናዊ ቅኝ
ገዢዎች ምንኛ ፀረ አፍሪካ መሆናቸውን በዚሁ አሳይተዋል። ሉሙምባ ግን ሰው እ
ንጂ ስራውና ስሙ አይሞቱም ነውና እነሆ እስካዛሬ ህያውና አርአያ የአፍሪካ ጀግና
ሆኖ ቀጥሏል። የሉሙምባን ፅኑና ቆራጥ አቅዋም ከዛሬዎቹ የአፍሪካ ማፈሪያ የፖለ
ቲካ ሰዎች ጋር ለማነፃፀር ይረዳ ዘንድ ሉሙምባ ከመሞቱ በፊት ለሚስቱ ፖሊን ከፃ
ፈው ደብዳቤ በከፊል ትርጉሙ ከዚህ በታች ሰፍሯል፣

*" ዛሬ ባይሆን ነገ ሕዝቤ እንደ አንድ ሰው ሆኖ በመነሳት ሁሉንም የውስጥና የውጭ
ጠላቶች እንደሚያስወግዳቸው፣ ቅኝ አገዛዝንም ወግድ ብሎ ክብሩን በጠራች ፀሐይ
ስር እንደሚያስከብር ሙሉ ዕምነት አለኝ።*

*"ብቻችንን አይደለንም። አፍሪካ፣ እስያና ነፃ ሕዝቦች በሞላ ቅኝ ገዢዎችና ቅጥረኞ
ቻቸው ከኮንጎ ምድር እስኪወገዱ ድረስ ትግሉን ከማያቋርጡት ከሚሊዮኖች የኮንጎ
ተወላጆች ጎን ናቸው። ከዚህ በኋላ ምናልባትም ለማላያቸው ልጆቼ መልዕክቴ የኮ
ንጎ የነገ ዕጣ በነሱና በሁሉም ዜጋ ጥረት ላይ የተመሰረተ መሆኑንና አለ ክብር ምን
ም ነፃነት አለመኖሩን፣ አለፍትሕ ምንም ክብር እንደማይገኝና አለ ነፃነትም ነፃ ሰው
ሊኖር እንደማይችል (እንዲረዱ) ነው። ዱላና ድብደባ ሆነ ግበረ ሰየል መ ቼም
ቢሆን መቼ ምሕረት እንድጠይቅ አላረገኝም። ምክንያቱም መሰረታዊ መርሆዎቼን
ክጄና ተንንብሼ ከምኖር አንገቴን ሳልደፋ፣ የማይበገር ዕምነቴንና በሀገሬ ብሩህ ነገ*

*ና ዕጣ ላይ ያለኝን ንቅንቅ የማይል እቅዋም ሳልቀይር መሞትን እመርጣለሁ:: ታሪ
ክ አንድ ቀን ፍርዱን ይሰጣል፣ግን ይህ ታሪክ በብሩስልስ (የቤልጅም ዋና ከተማ--
ሁቱ) ፣ በፓሪስ፣ በዋሺንግተንና የተባበሩት መንግስታት የሚነገር ሳይሆን ከቅኝ ገዢ
ዎችና አሽከሮቻቸው ነፃ በወጡ ሀገሮች የሚለፈፍ ይሆናል:: አፍሪካ ከሰሜን እስከ
ደቡብ የክብርና የድል ታሪኳን ትፅፋለች:: ውድ ባለቤቴ ለኔ አታልቅሺልኝ:: መከ
ራ እየተቀበለች ያለችው ሀገሬ ኮንጎ ራሷን መከላከልና ነፃነቷንም ማስከበር እንደም
ትችልና እንደምታውቅም እኔ አምናለሁ:: ኮንጎ ለዘለዓለም ትኑር! አፍሪካ ለዘለዓለ
ም ትኑር! "*

በሀገሩ ሕዝብ ላይ ሙሉ ዕምነትን ይዞ፣ ከጭቃ በወጡ ቅጥረኞች ተንግላቶ በጫካ በ
ሌሊት በጥይት ተገደሎ ሬሳውም ተቆራርጦ ቢጣልም የሉሙምባ ታሪክ ሕያው ሆኖ
አለ :: ምሕረት ጠይቀን፣ አቅዋም ቀይር ወዘተ በሚልም ባዕዳን ሊያስጎነብሱት፣
ሊደልሉት-- ሊገዙትም ወይም ሊያስፈራሩት ሲጥሩ ወግዱ ብሎ ተፍቶባቸው ሞት
ን ተቀበለ እንጂ ሉሙምባ ሕዝብንም ሀገርንም ራሱንም አላዋረደም::

ይህ አርአያነቱ ዛሬም የኮንጎን ብቻ ሳይሆን መላ የአፍሪካ ሕዝብን ቀስቃሽ ነው:: ባ
ዕዳኑ ግን ሉሙምባን ገድለውና ቅጥረኞቻቸውን እነ ሞቡቱን ለስልጣን አብቅተው
ኮንጎን በጋራ ሲዘርፉ ቆዩ:: በኮንጎውም የርስ በርስ ጦርነት የኢትዮጵያ ወታደሮች
ሚና በአሜሪካ ቁጥጥር ስር በነበረው የተባባሩት መንግስታት ሽፋን የአሜሪካንን
ተልዕኮ ማስፈፀም ነበር:: በኮንጎና በሉሙምባ ላይ የደረሰው አፀያፊ ድርጊት፣ ዘለዓለ
ም መወገዝ ያለበት ወንጀል ነው:: ታሪክን የረሱ ምን ያህል ባዕዳኑ አፍሪካንን ጎድተ
ው አሁን ላለንበት አሳዛኝ ሁኔታ እንዳበቁን መረዳት ይሳናቸዋል:: አሜሪካ ነፃ ሲያ
ወጣቸው፣ ለዓለም ሕዝብ ብሎ ሌሎች ሀገሮችን (ኢራቅ፣ አፍጋኒስታን ወዘተ ) ሲወ
ርና ሲሞትላቸውም ይታያቸዋል:: ቀጣይና ጎጂ ሞኝነት:: እንግሊዝና አሜሪካ በዓለ
ም አቀፍ ደረጃ ያደረሱትን ጉዳት ትተን ወደ አፍሪካ ፊታችንን ስናዞር የፈፀሙብን
ወንጀል ከባድ መሆኑን እንገነዘባለን:: የጄኔራል መንግሥቱና የገርማሜ ንዋይ የታህ
ሳሥ 1953 መፈንቅለ መንግሥት ከነበረው የራሱ ጉድለት አልፎ የአሜሪካው አምባ

ሳደር ኤድዋርድ ኮሪ ከጦር ሰራዊቱ ጄኔራል መርዕድ ጋር በመሆን መፈንቅሉን ለማ
ክሸፍ ከፍተኛ ሚና ተጫውቷል:: የጋናውን ንክሩማህ የገለበጡት እነሱ ናቸው:: ሚ
ልተን አቦቴ ንግግሩና አቅዋሙ ወደ ግራ ዘንበል አለ ብለው ያን አረመኔ ኢዲ አሚ
ንን በሕዝብ ላይ ያመጡ እነሱና እስራኤል ናቸው:: ፈረንሳይም በበኩሏ ነፃ ቢወጡ
ም ግዛቶቼ በምትላቸው የአፍሪካ ሀገሮች ግፍ ፈፅማለች:: የአልጄሪያ ሕዝብ ላይ ያ
ደረሰችው ፍጅት እንግሊዝ ማኡ ማኡን እንቅስቃሴ ለማውደም ከፈፀመው ጭፍጨ
ፋ የሚተናነስ አይደለም:: ካሜሩን ነፃ ሊወጣ ሲል ቅጥረኞቸውን አህማዱ አሂጆን ለ
ስልጣን ለማብቃት ስትል ፈረንሳይ ሀገር ወዳዱን ፓርቲ ዩፒሲን አጥቅታ መሪውን

ሩብን ኡም ንዩቤን መግደሏ አልበቃ ብሎ እሱን የተካውን ፌሊክስ ሙሜን ጄኔቫ ከ ተማ ቡና ቤት በመርዝ ገድላለች፡፡ ሙሜን የተካውም እርነስት ኡዋንዴም ተገድሏ ል፡፡ በፈረንሳይ ድጋፍ የቻዱ ቶምቦልባይ የፍሮሊና አማፅያንን ሊያጠቃ ሲችል ዛሬ በስልጣን ያለውም ኢድሪስ ዴቢ ከዓመት በፊት ከውድቀት የዳነው በፈረንሳይ እርዳ ታ ነው፡፡ ከሁሉም በላይ ደግሞ ምዕራባውያን የአፓርቴይድን አገዛዝ ሙሉ በሙሉ ደግፈው ማንዴላንም በሽብርተኝነት ያወግዙ እንደነበር የምናስታውሰው ነው፡፡

ዛሬ መላ አፍሪካን ስንቃኝ ከጥቂት ቦታዎች በስተቀር አህጉራችን ለባዕዳን በተሸጡ አምባገነኖች ስር ወድቃ ለጭፍን ብዝበዛም መዳረጓን መታዘብ እንችላለን፡፡ መለስ ተባለ ቦንጎ ተባለ ኪባኪ ገሌህና ቢያ ወይም ሙባረክ ተልባ ቢከፍቱት ናቸው፡፡ ደህ ና ጀመሩ ተብለው የነበሩት የዩጋንዳው ሙሴቬኒ፣ የአንጎላ ዶስ ሳንቶስና ሙጋቤም ቢሆኑ ያው የተለመደው አምባገነን ከመሆን ማምለጥ አልቻሉም፡፡ በመሆኑም የጀግ ናውን ፓትሪስ ሉሙምባ 50ኛ የሙት ዓመት ስንዘክር አፍሪካ ምንኛ ጀግና ልጆች አጥታ ለቅጥረኞች መጋለጧን መታዘብ እንገደዳለን፡፡ ሞት አይፈሬዎቹ አልቀው ሆ ድአምላኩዎቹ፣ ከወንዝ ገብተው የሚያልባቸው ፈሪዎቹኢትዮጵያንም አፍሪካንም የ ሞሉ ይመስላል፡፡እንደሚባለው ያኔ ያኔ ሰውም ሰው ነበር፣ ወርቁም በመዳብ አልተ ተካም ነበር፡፡

ዛሬ ዛሬ ደግሞ ጊዜው የመለስ ዓይነት ቡከኖች ወይም የሕዝብን ትግል መራን ብለ ው ወዲያውኑ ደፋና ጎንበስ ባዮች የሞሉበት ሆኗል፡፡ ለዚህም ነው ሕዝብ የራሱንና የሀገሩን ዕጣ በእጁ ለማስገባት ሰሞኑን በቱኒዝያ እንደታየው ሁሉ ቆርጦ መነሳት ያ ለበት፡፡ በቱኒዝያ፣ በአልጄሪያ በግብፅና ሞሪታንያ ራሳቸውን ያቃጠሉት ወይም ሊያቃጥሉ የሞከሩት የትግል ክብሪቶችም ምሳሌ ናቸው፡፡ ታሪክም አልዋሸ ሰውም አልተበላሸ ብለን ለትግል ለመነሳት ያብቃን፡፡

የፓትሪስ ሉሙምባና ሌሎች ጀግኖች መስዋዕትነትና አርአያነት አይረሳም!